

# ያዕቆብ

- ያዕቆብና ኤሳው መንትያዎች ነበሩ። ሆኖም ኤሳው የበኩር ልጅ ነበር። የበኩር ልጅ እንደመሆኑ መጠን ደግሞ ከወንድሙ ጋር ከሚወርሱት ከአባታቸው ርስት በርከት ያለውን የመውረስ መብት አለው።

- ያዕቆብ ብዙ ጊዜውን የሚያሳልፈው በወላጆቹ ድንኳን አካባቢ አንዳንድ ስራዎችን እየሰራ ነበር። ኤሳው ግን አዳኝ ነበር። ያዕቆብ ለስላሳ ገላ ሲኖረው ኤሳው ግን መላ ሰውነቱ በፀጉር የተሸፈነ ነበር።

- አንድ ቀን ያዕቆብ ወንድሙን ኤሳውን በማታለል የብኩርናመብቱን ወሰደበት። ይህንንም ያደረገው ኤሳው በጣም በተራበበት ሰዓት ነበር። ታዲያ በጣም የተራበው ኤሳው ወንድሙን ያዕቆብን ሲያበስለው ከነበረው ምግብ እንዲሰጠው ይጠይቀዋል። ያዕቆብ ግን ኤሳው ብኩርናውን ሊሸጥለት ካልተስማማ እንደማይሰጠው ይነግረዋል። በዚህ መንገድ ያዕቆብ የኤሳውን ብኩርና ወሰደበት።

- ከዚያም አንድ ቀን ይስሓቅ ልጁን ኤሳውን ሊባርከው ፈልጎ በመጀመሪያ አድኖ ከሚያመጣቸው እንስሳት የሚወደውን ምግብ እንዲያዘጋጅለት ይጠይቀዋል። ታዲያ ይህን የሰማችው እናታቸው አባትዬው የሚፈልገውን ምግብ ታዘጋጅና ለያዕቆብ ትሰጠዋለች። በእጁና በአንገቱ ላይም የፍየል ቆዳ ታለብሰዋለች። በተጨማሪም ከኤሳው ልብሶች መካከል ትመርጥና ያዕቆብን ታለብሰዋለች። ይህም ወደ አባቱ ይስሓቅ ለምርቃት ሲቀርብ ኤሳውን ለመምሰልና አባቱን ለማታለል እንዲረዳው ነው። ይህም ተንኮላቸው ሰራ። ያዕቆብ አባቱን አታሎ የወንደሙን ምርቃት ተቀበለ።

❋ ኤሳው ከአደን ተመልሶ ይህን የወንደሙን ድርጊት በሰማ ጊዜ እጅግ ተቆጣ። ስለዚህ ያዕቆብ የነበረው ምርጫ መሸሽ ብቻ ነበር። አለበለዚያ ወንድሙ ኤሳው እጅግ ስለተበሳጨ ይገድለዋል። ያእቆብም በመሸ ጊዜም ድንጋይ ተንተርሶ ተኛ።

❋ ሕልምንም አለመ። ባየው ሕልምም መሰላል ከምድር እስከሰማይ ድረስ ተዘርግቶ መላእክት በመሰላሉ ወደላይና ወደታች ሲወርዱና ሲወጡ ተመለከተ። ከመሰላሉ ጫፍ ላይ እግዚአብሔር ነበረበት። እግዚአብሔርም

❋ ያዕቆብን ከክፉ ሁሉ እንደሚጠብቀውና ትልቅ ቤተሰብ እንደሚሰጠው፣ እንዲሁም አሁን ያረፈበትን ምድር እንደሚያወርሰው ቃል ገባለት።

❋ ከእንቅልፉ ሲነቃም ለእግዚአብሔር ሰገደ። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነም ከሚያገኘው ከማናቸውም ነገር አንድ አስረኛውን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ቃል ገባ።

❋ ከዚህ በኋላም ያዕቆብ ሚስቶችን አግብቶ አስራ ሁለት ልጆችን ወለደ። ስሙም እስራኤል ተባለ። ቤተሰቦቹም አስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ተብለው መጠራት ጀመሩ።

የያዕቆብና የኤሳው ታሪክ በመፅሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት መፅሓፍ ከምዕራፍ 25 እስከ ምዕራፍ 27 ድረስ ይገኛል።

http://gardenofpraise.com